# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

## አዲስ አበባ

## መመሪያ ቁጥር ኤፍኤክስ ዲ/30/2006

## ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ገንዘብ የመላክ አገልግሎትን በተመለከተ የወጣ መመሪያ

በኢትዮጵያ ያለውን መደበኛ የሆነ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ገንዘብ የመላክና የማስተላለፍ ሂደት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም የመላኪያውን ወጪ በመቀነስ፣ ገንዘብ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚልኩ ግለሰቦች ብቁ፣ አስተማማኝ፣ ፈጣን እና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በብሔራዊ ባንክ በኩል የወጣ ከውጭ ወደ ሀገር የሚላክ ገንዘብን በተመለከተም ሆነ ሂደቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል ጥርት ያለና ዝርዝር መመሪያ ባለመኖሩ፣

ስለሆነም በገንዘብና ባንክ አዋጅ ቁጥር 83/1994 አንቀፅ 6 እና 61 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ /ከዚህ በኋላ "ባንኩ" እየተባለ የሚጠራው/ ይህን መመሪያ አውጥቷል::

### አንቀፅ 1
### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ ካልሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ:-

1.1. **"በዜጎች ወደ ሀገር የሚላክ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር"** ማለት በውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ወይም በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ ዜጎች ወደ ሀገር ውስጥ /ኢትዮጵያ/ የሚልኩት ገንዘብ ማለት ነው:: ይህ የገንዘብ ዝውውር ከዚህ በታች ያሉትን ያካትታል:-

ሀ. የግል ዝውውር (Personal transfers)

ለ. ለኢንቨስትመንት፣ ለበጐ አድራጐት፣ ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ለማስገባትና ለአገልግሎት ክፍያዎች የሚውል ገንዘብ

ሐ. ጊዜያዊና ቋሚ ስደተኞች የሚያስተላልፉት ገንዘብ (migrant transfers)

1.2. **"ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት"** ማለት ደንበኞች ወደ ሌላ ቦታ ገንዘብ እንዲልኩ ወይም እንዲቀበሉ የሚያስችል አገልግሎት ነው::

1.3. **"ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጭዎች"** ማለት ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች ሲሆኑ ለደንበኞቻቸው ገንዘብ የመላክ አገልግሎትን በቀጥታ በባንኮች በኩል ወይም በገንዘብ አስተላላፊ ወኪሎች አማካይነት ከባንኮች ጋር በመተባበር የሚሠሩ ናቸው:: ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ያካትታል:-

1.3.1 ዓለም አቀፍ የገንዘብ አስተላላፊዎች፣

1.3.2 የንግድ ባንኮች /በስዊፍትና ሌሎች መንገዶች ገንዘብን ከባንክ ባንክ የሚያስተላልፉ/

1.4. **"የገንዘብ አስተላላፊ ወኪል"** ማለት በውጭ ሀገር የተሰጠ ህጋዊ ፈቃድ ያለውና ከሀገር ውስጥ ባንኮች ጋር በመተባበር ወይም ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚያወጣቸው ዝርዝር መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ወደ ሀገር የሚላክ ገንዘብን የሚቀበል ወይም የሚልክ የንግድ ድርጅት ነው::

1.5. **"የባንክ መለያ ኮድ"** ማለት የገንዘብ ተቋሙን ለመለየት በቴሌኮሚዩኒኬሽን መልእክት ግንኙነት ጊዜ የሚያገለግል ልዩ አድራሻ ነው::

1.6. **"የዓለም አቀፍ የባንክ ሂሣብ ቁጥር"** ማለት በኮረስፖንዳንት ባንክ የሚገኘውን ሂሣብ የሚለይ ልዩ የኮድ መለያ ነው::

1.7. **"የብቸኛ አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ"** ማለት አንድ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅት ወኪሎቹን ወይም ከርሱ ጋር የሚሠሩትን ሌሎች የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶችን ከርሱ ውጭ ለሌላ  የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅት አገልግሎት እንዳይሰጡ የሚከለክልበት ሁኔታ ነው::

1.8. **"መገኛ ጣቢያ"** ማለት ተጠቃሚዎች ስለሚላክላቸው ገንዘብ መረጃ የሚያገኙበት ጣቢያ ሲሆን የባንኩ ቅርንጫፍ፣ ፖስታ ቤት፣ ድረ ገፅ፣ መፅሔት፣ ስልክ ... ወዘተ ሊሆን ይችላል::

1.9. **"የንግድ ባንኮች"** ማለት በሀገር ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸውና ለአስቀማጮች፣ ለተበዳሪዎች እና ለገንዘብ ላኪዎች እና/ወይም ተቀባዮች የመሀል ላይ አገናኝነት አገልግሎት የሚሰጡ የንግድ ድርጅቶች ናቸው::

1.10. **"ፋይናንስ ነክ የሆኑ አገልግሎቶችን የማይሰጡ ድርጅቶች"** ማለት በውጭ ሀገር ያሉ ቅርንጫፍ ጣቢያዎቻቸውን በመጠቀም ወደ ሀገር ውስጥ ገንዘብ በማስተላለፍ አገልግሎት ላይ እንዲሰማሩ ፍቃድ የተሰጣቸው የንግድ ድርጅቶች ናቸው:: እነርሱም:-

   ሀ. የኢትዮጵያ አየር መንገድ

   ለ. የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ናቸው::

1.11. **"ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር አከናዋኞች"** ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸውና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የንግድ ተቋማት ሲሆኑ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር አገልግሎትም ይሰጣሉ::  እነዚህም ዌስተርን ዩንየንን፣ መኒ ግራምን፣ ማኒፍሎን፣ አደም ፈንድስን ... ወዘተ ያካትታል::

## አንቀፅ 2
## ዓለም አቀፍ ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎትን መስጠት የሚችሉ

2.1. የሚከተሉት ተቋሞች ወይም ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በዝቅተኛ ዋጋ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ማስተለለፍ አገልግሎት ለመስጠት ይችላሉ::

   2.1.1 ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር አከናዋኞች ከንግድ ባንኮች ጋር በመተባበር

   2.1.2 የንግድ ባንኮች

   2.1.3 ፋይናንስ ነክ የሆኑ አገልግሎቶችን የማይሰጡ ድርጅቶች

## አንቀፅ 3
## ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጪዎች ያሉባቸው ግዴታዎች

3.1. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጡት አገልግሎት ለደንበኞች ግልፅ መሆን አለበት:: ለዚህም ሲባል ገንዘብ አስተላላፊዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በግልፅ ማሳወቅ ወይም መለጠፍ አለባቸው::

3.1.1. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስቀምጧቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እና ወጪዎች ለምሳሌ የኮረስፖንዳንት ባንኮችን እና የወኪሎቻቸው ክፍያ እንዲሁም የሚሰጧቸውን የተለያዩ አይነት አገልግሎቶች፣

3.1.2. ገንዘቡ ለተቀባዩች ለመድረስ በግምት የሚፈጅበት ጊዜ እንዲሁም የምንዛሪውን ተመን፣

3.1.3. የኮረስፖንዳንት ባንኮቻቸውን የባንክ መለያ ኮድ እና ዓለም አቀፍ የባንክ ሂሣብ ቁጥር::

3.2. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ለመስጠት የሚደረጉ የውክልና ስምምነቶች እንዲሁም በዚያ ውስጥ የሚገኙ አንቀፆች በነፃ የውድድር ስርዓት ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው:: ስለዚህም

3.2.1. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጪዎች የውክልና ስምምነት በሚያደርጉበት ጊዜ የብቸኛ አገልግሎት ቅድመ ሁኔታን ማስወገድ አለባቸው::

3.2.2. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት በሚሰጡ ድርጅቶች መካከል የሚደረግ የውክልና ውል ስምምነት ከሁለት ዓመት ገዜ መብለጥ የለበትም:: ነገር ግን የውክልና ውሉ የብሔራዊ ባንክ ይሁንታ በማግኘት ሊታደስ ይችላል::

3.2.3. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጪዎች በገንዘብ ማስተላለፍ አገልግሎት ላይ ዜሮ ወይም ትንሽ ታሪፍ መጣል አለባቸው:: ገንዘብ ለመላክ የሚያስከፍሉትን ክፍያም ከሚያደርጉት ለውጥ ጭምር ለብሔራዊ ባንክ ማስታወቅ አለባቸው::

3.2.4. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጪዎች ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር አከናዋኞች ጋር አዲስ የውክልና ስምምነት ከመግባታቸው በፊት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው:: ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ሰጪዎች ይህን የውክልና ስምምነት ፈቃድ ከተሰጣቸው የገንዘብ ዝውውር አከናዋኞች ጋር ብቻ ማድረግ የሚገባቸው ሲሆን፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሠነዶችም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለባቸው::

ሀ. በውጭ ሀገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ድርጅቶች የተረጋገጠ የገንዘብ አስተላላፊ ወኪሉ ህጋዊ ሰነድ

ለ. ረቂቅ የውል ስምምነት

ሐ. የተሻሻለው ረቂቅ ስምምነት

3.2.5. ንግድ ባንኮች የሲዊፍት (SWIFT) ዘዴን በብቃት ለገንዘብ ማስተላለፍ አገልግሎት መጠቀም አለባቸው::

3.2.6. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ ባንኮች የገንዘብ መላክ አገልግሎት በተቀላጠፈ መልኩና በ24 ሰዓታት ጊዜ ውስጥ መስጠት እንዲያስችላቸው ለዚህ ሥራ ብቻ የተመደበ የሥራ ክፍል መክፈት አለባቸው::

3.2.7. ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች፣ የባንክ መለያ ኮዳቸውንና ዓለም አቀፍ የባንክ ሂሣብ ቁጥራቸውን በበራሪ ፅሑፍ፣ በድረገፅ እና በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቆንስላዎቻቸው በኩል ማስተዋወቅ አለባቸው::

## አንቀፅ 4
## ወደ ሀገር ውስጥ የተላከውን ገንዘብ የሚያሳይ መረጃ ስለማቅረብና ምርመራ

4.1. ባንኮች እንዲሁም ሌሎች ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ወደ ሀገር ውስጥ የተላከውን ገንዘብ የሚያሳይና ከዚህ ጋር በተያያዘው ፎርም መሠረት የተዘጋጀ ሪፖርት በማቅረብ ስለ አፈፃፀሙ ለብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬና ስታስቲክስ እና ቁጥጥር መምሪያ በየወሩ ማሳወቅ የሚኖርባቸው ሲሆን ዝርዝሩም በመንግሥት፣ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በግለሰቦች፣ ኃላፊነታቸው በተወሰነ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ስም የተላከውን ገንዘብ የሚያሳይ መሆን አለበት::

4.2. ባንኮችም ሆኑ ሌሎች የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ያሉ የፋይናንስ ነክ አገልግሎቶችን የማይሰጡ ድርጅቶች ወደ አገር ውሰጥ ያስገቡትን የውጭ ምንዛሪ መጠን በየወሩ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው::

4.3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም ጊዜ ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ወደሚሰጡ ድርጅቶች ዘንድ በመሄድ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል:: ይህ ምርመራ በዚህ መመሪያ እንደተገለጸው የገንዘብ ማስተላለፍ አገልግሎትን በተመለከተ በእያንዳንዱ የመገኛ ጣቢያ መረጃዎች በትክክል መገለጻቸው መመልከትን ያካትታል::

## አንቀፅ 5
## ቅጣት

ማናቸውም ገንዘብ ወደ ሀገር የመላክ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም የዚህን መመሪያ ማናቸውንም አንቀፅ ጥሶ ሲገኝ የባንክ አገልግሎትን ፈቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር በወጣው መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ 27/2001 መሠረት ተገቢው ቅጣት ይጣልበታል::

## አንቀፅ 6
## ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 22 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል::

ተክለወልድ አጥናፉ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ